# አስናቀች ወርቁ--የማትጨልም ኮከብ!

ሀማ ቱማ

አንዳንድ ፍጡሮች የተሰጣቸውን ጊዜ ሳይጠቀሙበት በድን ሆነው ከርመው ይሞታሉ፡፡ ሸክም ሆነው፣ ዓለምን ላይገዙላት ቆርጠው መነሳት አቅቷቸውና ለጊዜ ሰግደው፣ ተንበርክከው በታሪክና ጊዜ  መዝገብ ውስጥ ማህተማቸው ደብዘዛ፣ ሚዛናቸውም የጤዛና የገለባ ሆኖ ያልፋሉ፡፡ በመሞታቸው አያጎድሉም--የጳጉሜ ውዝፍ አንሳ ሰለባዎች ዓይነት ናቸው፡፡  ሌሎች  ደግሞ ሲወለዱ እንደ ማነኛወም ሕፃን ቢያለቅሱም፣ መኖርን ደፍረው፣ በፈለጉት መስክ አለና ብለው፣ አምፀው፣ ጊዜን ገርተው ህይወታቸውን ኖረውበት፣ ቀናቸው   ሲደርስ  ይለዩናል፡፡    አስናቀች ወርቁ በጊዜዋ ኖራበታለች፣ ወግ ተብዬውንም ጥሳ ለዘመናዊ ሴቶች ሁለ ፈር ቀዳለች፣ በድፍረቷና እንደፈለገችና እንደ አሰኛት ለመኖ




ር በመቁረጥዋ የሁላችንንም አድናቆትም አትርፋለች፡፡ አስናቀች  ስትለየን በመሀላችን የሚፈጠር ሰፊ የእጦት ስሜትና ሀዘን አለ ፡፡ ተኪ የለሽ ናት፣ ቅርሷ ቅርሳችን ነው፡፡

ለዓመታት ታማ ሳለች ግን ሊረዷት የሚገባቸው ዜጎች (ከዘረኛውና ፀረ ኢትዮጵያው ወ
ያኔ እንኳን ይህ ሀገራዊ የህላፊነት ስሜት አይጠበቅም!) ሊታደጓት ዝግጁ ባለመሆናቸ
ው በጋራ እናፍራለን፡፡ በሜሪ አርምዴ ሕመም ጊዜ፤ በብዙነሽ በቀለ ጊዜ፤ አልፎም ሎሬ
ት ፀጋዬንም በተመለከተ ያጋጠመን መሳቀቅ ነው፡፡ የተረሱ የፖለቲካ እስረኞችና ረጂ ያ
ጡ የሰማዕት ቤተሰቦችን ፈርዶባታልና ሀገራችንን ህላፊ አድርገን እንውቀሰና ኢትዮጵ
ያ ነብርን በጫንቃ፤ወርቅን በጭቃ ከሆነች ዘመን አልፏል እንበላት--የገደሏት እየታቀፉ
ና ሰገነት እየወጡ፡፡ የሞቱላትና ስሟን ያስጠሩት እየተረሱ፡፡ ስንቱ ነፍሰ ገዳይ አይደል
ዛሬ ክቡር ዜጋ ተብሎ የሚውገረገረው! ስንቱ በደም የተጨማለቀ፤ ዜጎችን የሸጠ፤ ሀገር
ን ለባዕድ አሳልፎ የሰጠ ወራዳ አይደል አንቱ የተባለው? የዘንድሮ ዜጋ--በተለይም በው
ጭ ሀገር ያለው -- ጀግና ብሎ የሚያደንቀው፤ ቅርሳችን ብሎ የሚያከብራቸው
እውነትም ለዚች ሀገር ከፍ ያለ አስተዋፅዖ ያደረጉትን ወይም ውድ ሕይወታቸውን
እስከመስጠት የደረሱትን ሳይሆን ነጋ ጠባ ከመ እስስት ቀለማቸውን እየቀየሩ፤ አቅዋ
ማቸውንና ሰብዕናቸውን እንደ እርያ ከጭቃ
እየከተቱ፤ አስመሳይና ፈሪሳዊ የሆኑትን ማዳ
ነቃቸውን መታዘባችን አልቀረም፡፡ አስናቀች
ግን እስከመጨረሻው ተወዳጅ ያደረጋትን ፈገ
ግታና ብርታት፤ ሕይወትን በሁለት እጆቿ
ጨብጣ ለጊዜ እጅ አልሰጥ ብላ እንደቆየች
ታዛቢዎቸ ሰሞኑን መሰከረዋል፡፡ ሞትን ሞታ
አልጠበቀችውም፡፡



አስናቀች በ25 ሳንቲም ክራር ገዝታ ዝነኛው
ን እንደ ኢሩሳሌም ዘፈን ፅፋ ከዘፈነች
ከሀምሳ ዓመት በላይ አልፏል፡፡ የተወለደች
ው በገዳም ሰፈር አካባቢ በእኛው አቆጣጠር
በ1926 ዓ.ም. ነበር-- የያኔ ስሙኒ ዋጋው ቀላል አልነበረም፡፡ አስናቀች በልጅነቷ
እናቷ በመሞታቸው መጋፈጥ የነበረባት ኑሮ ከባድ ነበር፡፡ ግን ወጣቷ የማትበገር
በመሆኗ ኑሮን ተጋፍጣ፤ ፍላጎቷን ለማሟሏት ችላለች፡፡ ከአሳዳጊዋ ከክርስትና እናቷ
ጋር የነበራትም ግንኙነት መልካም ስላልነበር እህቷ ዘንድ (አንድ አክስቷ ጋ በመጨረሻ
ተረጋግታ መኖር እስከትችል ድረስ) ለተወሰነ ጊዜ ተቀምጣ እንደነበርም ተነግሯል፡፡
የቄሰ ትምህርት ቤትን ጨርሳ በጊዜው በነበረው አንድና ብቸኛ የሴቶች ትምህርት
ቤት--እቴጌ መነን-ልትገባ ፈልጋና ከዳይሬክተሯ ከወይዘሮ ስንዱ ገብሩ (እሳቸውም
የመጀመሪያዋ ሴት የፓርላማ አባል ለመሆን - በ1957 - በቅተዋል) ፈቃድ ካገኘች
በኋላ ለህክምና ምርመራና ለዩኒፎርም ገንዘብ መክፈል ባለመቻሏ የዘመናዊ ትምህርት
ዕድሏ በዚያው አብቅቷል፡፡ ይህም ለሀገራችን ኪነት--ዘፈንና ቲያትር-ጥሩ አጋጣሚ

ሆነ ማለትም እንችላለን፡፡ አስናቀች በአብዛኞች ግምት ቆንጆ የምትባል ወጣት ስለነበረ ችም (ቅላቷ የፈረንጅ ነበር የሚሉ ብዙ ነበሩ፤ ቀይ መሆን ቆንጆ መሆን ይባል ነበርና) ይህም ብዙ ዕንቅፋቶችን ፈጥሮባት ነበር፡፡ ባለስልጣኖች ሳይቀሩ ያስቸግሯት እንደ ነበር የታወቀ ነው፡፡ በነበረው የዘመኑ ወግ አጥባቂ አቅዋም ሴት ልጅ ሲጋራ ካጤሰች፤ መጠጥ ከጠጣች፤ ወደ መድረክ ከወጣችና ከደነሰች፤ ቡና ቤት ተቀጥራ ከሰራች ወዘተ ባለጌ የሚያሰኝ ነበርና ክልክል የተባሉትን ሁሉ አስናቀች ስላደረገችና ስለሆነች፤ ከሜ ሪ አርምዴ በመለስም በይፋ የማይባለውን አስገብታ ትዘፍንም ስለነበር በአሉታዊ ትላንትም ዛሬ ገምግመው ታላቅ አስተዋፅዖዋን ሊያሳንሱ የሚምክሩ ነበሩ፤ አሉም፡፡ ድካም ከንቱ፡፡

አስናቀች የክራር ንግስት የሚያሰኛትን ችሎታ እያሳደገች በመሄድ ላይ ሳለች ዕይታዋ ወደ ቲያትር በመዞሩ በሰፊው በሕዝብ ዓይን ልትገባ ቻለች፡፡ ለዚህም መድረክ የሆናት በ1939 የተቋቋመውና በማዘጋጃ ቤት ስር ሆኖ ከአራዳ ዘበኛና ሌሎች ሰፈሮችም የቲያ ትር ተጫዋቾችን ማሰልጠን የጀመረው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቲያትር ቤት (ዛሬ ብሔ ራዊ ቲያትር የሚባለው) ተቋም ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ሴቶች በቲያትር መድረክ ወጥተው መታየታቸው የሚፈለግ ባለመሆኑ የሴቶችን ሚና ወንዶች እንደ ሴቶች ለብሰውና ድም ፃቸውንም አቅጥነው ያሚሉ፤ ይጫወቱ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ግን በአስናቀች የቲያትር ተዋና ይነት ተቀየረ፡፡ ታሪክ ሊያስታውሰው የሚገባው ተስፋዬ ተሰማ በማዘጋጃ ቤቱ ሀላፊነት ሹመትን ካገኘ በኋላ ከጓደኛው ከአስፋው ተፈራ ጋር ለፃፈው የፍቅር ጮራ ቲያትሩ የ አበባን ቦታ ይዛ የምትጫወት ሴት ፍለጋ ገባ፡፡ ኮከብ አስናቀችም ፈነጠቀች፡፡ አስናቀች አበባን ሆና ስትጫወት ያለው ተመልካች ሁሉ ታሪኩ አሳዛኝ ድራማ ነበርና ዕንባ በዕንባ ሊራጭና ሊያደንቃትም በቃ ፡፡ በ1948 ዓ.ም.ና ከዚያም በኋላ የኦቴሎን ዴዝዴሞና ሆና፤ በሀኒባል፤ በዳዊትና ኦሪዮን፤ ወደ ክብር ጎዳና፤ ቴድሮስ፤ ስነ ስቅላት፤ እኔና ክፋቴ እና እናት ዓለም ጠኑ በተባሉት ሁሉ ውስጥ ተጫውታለች፡፡ የአስናቀች ችሎታ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ተመልካቾቾ ተጫዋችዋ አስናቀች መሆኗን እንኳን ሳያው ቁ ቲያትሩ የሚያልቅበት ጊዜም ነበር ተብሏል፡፡ የመጀመሪያዋ የመድረክ ሰው፤ የቲያ ትር እመቤትም ብትባል ተገቢ ነው፡፡ ከመድረኩ ጋር ልዩ ግንኙነት ነበራት--የፍቅር፤ የተግባባ ወዳጅ ውህደት፡፡ ሙዚቃ ን በተመለከተ ትችትና ትንተናውን ለአዋቂዎቹ ልተውና ለኔና ለብጤዎቼ ግን አስናቀች ኮከብ ነበረች፡፡ ደፋር፡፡ ለየት ያለችን ሴት አ ብሳሪና አንፀባራቂ፡፡ የዛሬ ወጣቶች ከአስናቀች ብዙ ሊማሩ ይችላሉ፡፡

በበኩሌ በመጀመሪያ አስናቀችን ማንነቷን ያወቅኳት በቲያትር ተጫዋችነቷ ነው፡፡ ተማ ሪ ሳለን በትምህርት ቤት ደረጃ ወደ ቲያትሩ ቤቱ ተወስደን ቲያትር እንድናይ ይደረግ ነበር (ለምሳሌ ቴድሮስን በቲያትር፤ በሲኒማ ደረጃ ደግሞ ቤን ኸር የተባለውን ወዘተ)፡፡ ለጥቆም ክራር ስትጫወትና የወጣት ዕደሜያችንን ያጀቡትን ዘፈኖቿንም ለመስማትና

ለማድነቅ በቃን፡፡ አስናቀች፤ ሂሩት፤ ብዙነሽ፤ ጠለላ፤ ዘነበች ወዘተ እንደነ ጥላሁን፤ ዓለማየሁ እሸቴ፤ አሰፋ አባተ፡ ካሳ፤ ማህሙድ፤ ግርማ በየነ፤ ተዘራ፤ የዘራፌዋ ሸሸግ ቸኮል፤ እሳቱና ፍሬው፤ ምኒሊክና ሌሎቹ ሁሉ የወጣትነት ጊዜያችንን ያሳመሩልን፤ ለዘፈንና ዕንጉርጉሮም ያበቁን ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ሀገሬ መከታ ጋሻዬ ያሰኙን፡፡ እንደ ኢየሩሳሌም እንደ አክሱም ጽዮን የሚለውን ድምፅ የሌለን ሁሉ የቻልን መስሎ እንዘፍን ነበር፡፡ ድምፅ ፤ የክራርና የቲያትር ችሎታና የመኖር የመደሰት ረሀብ የነበራት አሰናቀች ከዚህ ሁሉ በላይ ግን በዘመኑ ወጣቶች አነጋገር ፍፁም ደባሪ አልነበረችም፡፡ ሶል ናት የምትባል ሴት ነበረች፡፡ ቄንጠኛ፡፡ ደርግን ትደግፍ አትደግፍ አላውቅም ግን ሀገሯን መውደዷን ብዙዎች ይመሰክራሉ፡፡ ሕዝብ ለሕዝብ በተባለውም ተካፍላ ችሎታዋን ለአዲሱ ትውልድ አስተዋውቃለች፡፡



አስናቀችን በአካል ያገኘኋት በፈረንጆቹ አቆጣጠር በመስከረም 1998 ዓ.ም. በፓሪስ ከ ተማ ነበር፡፡ ከተስፋዬ ገሰሰና ሌሎችም ጋር ሆና በመምጣት ሚሼል ላሪሰ በጎንደር የሚ ለውን ስለዛርና አስማት የሚያወሳው ቲያትር ውስጥ ዋና ተጫዋቾ ሆና፡፡ ጊዜና አኗኗሯ





በሰውነቷ ላይ ጥቃት ማድረሳቸው ቢታይም ሳቋና የአለና መንፈሷ የተነካ አልነበረም፡፡ በመድረክ ላይም ኢትዮጵያዊውም ፈረንጁም በሰፊው አጨ ብጭቦላታ ል፡፡ በቀጭንና ረጅም የሲጋራ መያዣ ከታ የምታጤሰው ሲጋራም ከቶም እጅ አልሰጥ

ማለቷን የሚያሳይ ነበር፡፡ አንዲት ብርጭቆ ውስኪም ለምን አይቼ ሳትል አጫውታና ለች፡፡ ዝርዝሩ ዛሬ ኪሰ ቀዳጅ ነው፡፡ አብራን የፓሪስ ከተማንም ለመጎብኘት ስትዞር ም ጨዋታዋ ሳቢና ማራኪ ከመሆኑ ሌላ እዚህ እዚያም የገዛቻቸው ልብሶችና ጫማ ዎች አልደክም ያለ የወጣትነት መንፈሷን የሚያሳዩ ነበር፡፡ “አርቲስት እኮ ነኝ፤ ዘመናዊ



እኮ መሆን አለብኝ፤ ሽክ ማለት አለብኝ ” ያለችውን ሁላችን እናስታውሳለን፡፡ ይህን የመስለ መንፈስና የደስታ ስሜት ያላት ሴት በበሽታ ለአልጋ ቁራኛ መሆኗን መስማት የሚያበሳጭ ነበር፡፡ ሆኖም እሷ በሁኔታዋ ሳታላዝንና በቀቢፀ ተስፋ ሳትዳከም እንደ አመጣጡ ይዛና ተቋቁማ መቆየቷንና ደስተኛ ነን ማለቷን መስማት ደግሞ የሚያስደስት ም የሚያኮራ ነበር፡፡ አስናቀች ሁሉን አስንቃ አልፋለች፡፡ ኮከብ ነበረች -- ዛሬም ያል ጨለመች ኮከብ ናት፡፡ በሀገራችን ታሪክ ውስጥ በተሰማራችበት መደረክ ባለችሎታ ሆናና ዙሪያዋንና ሁሉን አድምቃ በህይወታችን ውስጥ ቦታ በመያዟ ዕድለኞች ነን፡፡